# ትግላችን

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

ወርሃዊ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ
P. O. BOX 3198
103 64 Stockholm 3
SWEDEN

ቁጥር 2

ህዳር—ጥር 1963

ዋጋው፦ 1.50 ብር

## የመንግስቱን ጋዜጣ ስናገላብጥ

## "ሌሎች ጴጥሮሶች" ለምን?

የታወቁት ኢትዮጵያዊ ደራሲ አቶ ጸጋዬ ገብረመድህን ከጥቂት ወራት በፊት "ጴጥሮስ ያችን ሰአት" የሚል ታሪኳን የተመረኮዘ ትያትር አሰናድተው የአዲስ አበባ ከተማ ህዝብ ሊመለከት ቆይቷል::ባለፈው ሰሞንም እንደገና ቀርቦ ለህዝብ በመታየት ላይ ነው::ታሪኩን ሁላችንም እናውቀዋለን:: አቶ ጸጋዬ በዚህ ታሪክ ላይ በመመርኮዝ ተነስተው በአቀራረባቸው ሁለት አይነት ባህርይ ያላቸው ሁለት ሰዎች አገናኝተው ለማከራከርና ለማነጻጸር ይሞክራሉ::ባንዱ በኩል ታላቁ ኢትዮጵያዊ ጀግና አቡነ ጴጥሮስ "ለወራሪ ተገዥ፣ጊዜውን መስለው ይኑሩ" ቢባሉ አሻፈረኝ በማለት የክብር ኑሮንና የክብር ሞትን ይመርጣሉ::በሌላው በኩል ደግሞ ለገላ ጠባብና ጊዜያዊ ጥቅም በመስገብገብ አገሩን፣ክብሩን፣ነጻነቱንና ሰብአዊነቱን ፈጽሞ የረሳ "ጊዜው አስኪያልፍ መስሉ መኖር ይሻላል" በማለት የህይወት ፍልስፍናውን የተለም ሹምባሽ ባሻ አባ ገርሻ የተባለ ምስኪን ፍጡር ይገኛል::

ዛሬ ከታሪኩ 30 አመት ርቀን ጀግናውን ከከሀዲው መለየቱ ፍጹም ችግር የለውም::ጉዱ የሚፈላው በዛሬይቱ ኢትዮጵያችን በሚካሄደው ትግል ትንንቅ ውስጥ ጴጥሮስ የትኛው? አባ ገርሻስ የትኛው?ነው ብለን በመልክ በመልኩ ለመለየት የጀመርን እንደሆነ ነው::እንደምናየው አንዳንድ ጊዜ ነገሩ "ይዘበራረቅና" ወንበዴዎች ገዢዎችና "ጊዜው አስኪያልፍ መስሉ መኖር ይሻላል" ብለው በኢትዮጵያችን ተስፋ የቆረጡት አጨፋሪዎች "ጴጥሮስ ነን" ለማለት ይሞክራሉ::ከዚህም አከታትለው "ለውጭ የተገዙ" የሚሏቸውን የኢትዮጵያ ልጆች በአባ ገርሻ ለመመስል ቀላል ነው::

ከጥቂት ወራት በፊት ቲያትሩ ለመጀመሪያ ጊዜ ለህዝብ በቀረበበት ጊዜ "ሌሎች ጴጥሮሶች" ብለው በወጡት ርእስ

